# የአማራ ሕዝብ ማንነትና አስቂኙ

## የዘመኑ የትግሬዎች የ "ተጋሩ ነን!" ተረት!

በርካታ ሰዎች ባለሙያ ነን የሚሉትን ጨምሮ ነገሮችን በጥናትና በምርምር ሳይሆን በግምትና በመሰለኝ እውነት አስመስለው ማውራታቸው በተለይም ትግሬን በተመለከተ አብዛኛው ሰው የሚያስበው የተሳሳተና ትክክል ያልሆነ ነው፡፡ ትግሮች አሁን ትግራይ ተብላ በምትጠራው የሀገራችን ክፍል መኖራቸውን ብቻ በመመልከት ከመቸ ጀምሮና እንዴት እንደሆነ ሳያጤኑ አክሱማውያን መስለው የሚታዩት ሰው ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡

ከዓመታት በፊት "የዘር ማጥፋት ወንጀል በአማራ ሕዝብ ላይ በታሪክ ሒደት ከትናንት እስከ ዛሬ!" ፣ "አህያው ማን ነው? የሚመለከተውስ ብሔር አለን?" በሚሉ ርእሶችና ባለፈው ጊዜም "አማራ ትግሬና አህያ(አድጊ)!" በሚለው በሌሎችም በጻፍኳቸው ጽሑፎቸ ትግሮች ለምን ትግሬ (ተግሬ) እንደተባሉና ዐፄ ካሌብ የመን ከናግራን ክርስቲያኖች በተደረገላቸው የድረሱልን ጥሪ ከአይሁዶች መጠነ ሰፊ ጥቃት ሲታደጓቸው የመን በዘመቱና ድል አድርገው የናግራን ክርስቲያኖችን ከታደጓቸው በኋላ ሲመለሱ ዛሬ ትግሬ (ተግሬ) ብለን የምንጠራቸውን እዛው ከየመን ለባርነት በግዞት ያስገቧቸው መሆናቸውን, ለማረጋገጫም ትግሮች ከዓረቦች ከተለዩ ሩቅ ዘመን አለመሆኑን የሚያረጋግጡና ከዓረቦቹ ጋር ያላቸውን የቋንቋ የባሕል የሥነ ልቡናና የባሕርይንም አንድነት የሚያሳዩ መረጃዎችን በመዘርዘር ማስረዳቴ፣ እነዚህ ግዞተኞችን ለባርነት ለአገልጋይነት ከመግባታቸው ጋር በተያያዘ ማንነታቸውን ለመግለጽ ተግሬ (ተእግር ስር፣ መረገጫ፣ ባሪያ፣ አገልጋይ) የሚል ሥያሜ እንደተሰጣቸው፣ ትግሮች ይሄንን ታሪካቸውን በትውፊት ስለሚያውቁ "የመናውያን ነን" እንደሚሉ፣ ትግሬ በሚለው ሥያሜያቸው እንደሚያፍሩ እንደሚሸማቀቁ፣ በዚህ ሥያሜያቸው ከማፈራቸው ከመሸማቀቃቸው የተነሣም የብሔረሰብን ስም መጥቀስ ግዴታ ባደረገው የዘመኑ የወያኔ አገዛዝ የነዋሪዎች መታወቂያ ወረቀት ላይ እንኳን እንዳላሠፈሩትና የትግራይ መታወቂያ ብሔረሰብን የሚገልጽ ቅጽ እንደሌላው የሀገራችን አካባቢ ነዋሪዎች መታወቂያ የሌለው መሆኑን፣ ቢቸግራቸው ከጊዜ በኋላ "ትግራዋይ" የሚል አዲስ ቃል ለማስለመድ እየጣሩ ቢሆንም ሥርዎ ቃሉን ስላልለቀቀ "አልሸሹም ዞር አሉ" ከመሆኑ ውጪ ለውጥ የሌለው መሆኑን፣ ከትግሬ "ለሀገር ተቆርቋሪ ዜጋ ጨርሶ የለም!" ባይባልም ወላዊ ማንነታቸው ሲገመገም ግን ትግሮች ለዚህች ሀገር የጠላትነት ስሜት ያደረባቸውና እንደ አማራ የባለአደራነት የተቆርቋሪነት ስሜት የማይሰማቸው ከጥንት ጀምሮም ለምሳሌ በዐፄ ሠርፀድንግል ዘመነ መንግሥት ባሕረነጋሽ ይስሐቅ ሀገሪቱን ለመውረር ለመጡት ለቱርኮች በባንዳነት በማደር ሀገራቸውን ከድተው ባሕረነጋሹ ያሥተዳድረው የነበረውን ሰሜናዊ የሀገራችንን ክፍል ለቱርክ አሳልፎ በመስጠቱ ዐፄ ሠርፀድንግል ምጽዋ ድረስ በመዝመት ወራሪውን የቱርክ ሠራዊት፣ ከሐዲውን ይስሐቅንና ሠራዊቱን በ 1571 ዓ.ም መደምሰሳቸው ይታወቃል፡፡ ከዚህ ጊዜ በፊት ትግሮቹ ሀገራችን ከገቡ ጊዜ ወዲህ በዚያ በኩል የመጣ ወራሪ ኃይል አለመኖሩ ነው እንጅ ቢኖር ኖሮ ትግሮቹ ተመሳሳይ ክህደት ይፈጽሙብን እንደነበረ ከመጣው ወራሪ ኃይል ጋር ሁሉ እያበሩ ይህችን ሀገር ሲወጉ መቆየታቸው የሚያረጋግጠው ሀቅ ነው፡፡

ከባሕረ ነጋሽ ይስሐቅ ዘመን በኋላ የትግሮች ሐሳብ ሁሉ የመገንጠል ሆነ፡፡ ይሄንን ሐሳብ ለመፈጸምም ከወራሪ ከጠላት ጋር መዶለትና ተፈጻሚ ለማድረግ መጣር ሥራቸው አደረጉት፡፡ ገና ለገና "አንድ ቀን ይህ ሐሳባችንን ማሳካታችን አይቀርም!" በሚል እሳቤ ያሉበትን የሀገራችን ክፍል ከግራና ቀኝ ከታች ከግርጌም ማስፋፋት ተያያዙት፡፡ የመስፋፋቱ ዓላማ ምን እንደሆነ ያልገባቸውን የአጎራባች የአማራ ገዥዎችን በመደለል በማታለልና በማሳሳት ውል በመፈጸም ድንበራቸውን ለማስፋት ከድሮ ጀምረው ሥራየ ብለው የአማራ መሬቶችን ይጠቀልሉ ነበር፡፡ ለምሳሌ የቅርቡን ብናነሣ የትግሬ ገዥ የነበሩት ራስ ወልደሥላሴ በ 1801 ዓ.ም. አካባቢ በወሎ በኩል የወረሸዎች ገዥዎችን በጥቅም በመደለል የትግራይ ድንበር አለውኃ ድረስ እንዲሆን እንዲስማሙ ያደረጉበትን እጅግ አስተዛዛቢ ድርጊት ማንሣት ይቻላል፡፡ ትግሮች ይሄንን የውንብድና ስምምነት ይዘው ዛሬ ድረስ "ድንበራችን አለውኃ ነው! ክልላችን እዚያ ድረስ መከለል አለበት!" ሲሉ ይደመጣሉ፡፡
ትግሮች በዚህ ዓላማቸው ምክንያት ሥራየ ብለውም የቦታ ስሞችን ስም የነበረውን ስሙን በመቀየር ስም

ያልነበረውን አዲስ የትግርኛ ስም በማውጣት በሒደት ቦታው የትግሬ እንደሆነ ለማስመሰል ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ለምሳሌ በወልቃይት በኩል ሀገሬው ለምን እንደሆነ ሳይገባው ትግሮቹ ስም ላልነበራቸው ስፍራዎች እየተሽቀዳደሙ ትግርኛ ስም በመሠየም፣ አማርኛ ስም የነበራቸውን ደግሞ በስልትና በዘዴ ትግርኛ ስም እያወጡና ያም እንዲለመድ እያደረጉ ሀገሩ የትግሬ እስኪመስል ድረስ በትግርኛ ሥያሜዎች እንዲሞላ አድርገዋል፡፡ በሌሎች አጎራባች ስፍራዎችም ያለው ሁኔታ ተመሳሳይ ነው፡፡

እናም የትግሬ ተወላጅ ከሆኑ የሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ገዥዎች ከነበሩት አንድ እንኳን ሳይቀር በሙሉ ሀገሪቱን ለመገንጠልና ለማፍረስ የሚያሴሩ፣ ለዚህች ሀገርና ሕዝቧ የጠላትነት ስሜት ያደረባቸው ባንዶች ሆነው የሚገኙት ለዚህች ሀገር መሥዋዕትነት የከፈሉላት፣ የደከሙላት ካለመሆናቸውና ለባርነት የተጋዙ ከመሆናቸው ጋር በተያያዘ ባደረባቸው የጥላቻ ስሜት ኢትዮጵያን "የጠላት ሀገር!" ብለው በማሰባቸው ምክንያት እንደሆነም በዚያ ጽሑፍ ላይ ማስፈሬ፣ እንዲሁም ደግሞ የአክሱማውያን ነገሥታት ስሞችንም በመጠቃቀስ ወይ የግእዝ፣ የአማርኛ፣ የዕብራይስጥ የጽርእ ስሞች ናቸው እንጅ አንድም የትግርኛ ሥያሜ ያለው ንጉሥ ወይም ንግሥት አለመኖሩን፣ በቁፋሮ የሚገኙ ቅርሶችም ወይ በግእዝ ወይ በአማርኛ ለምሳሌ የዐፄ ኢዛናን (አብርሃን) የወርቅ የመገበያያ ገንዘብ ብናይ "አዘነ ነገሠ አከሰመ፣ ኢዛና ንጉሠ አክሱም ለማለት" እንደሚለው ወይ ደሞ በባዕዳን ቋንቋዎች የተጻፉ ናቸው እንጅ አንዲትም እንኳ ብትሆን የትግርኛ ጽሑፍ ተገኝቶ የማያውቅ መሆኑን፣ አማራ ነግሦ ከኖረበት አክሱምና አካባቢዋ ሊጠፋ የቻለው በሀገራችን እጅግ ግዙፍ ጥፋት እንዳደረሰች የወቅቱ የዓረብ ጸሐፍት ሳይቀሩ "ከነጋድያንና በዮዲት ጉዲት ተማርከው ወደ ዓረብ ሀገራት ለባርነት ከተሸጡ አማሮች ያገኘነው መረጃ" ብለው በማካተት ግዙፍ የሀገር ጥፋት እንዳደረሰች ከተናገሩላት ከጻፉላት የዮዲት ጉዲት ወረራ ጋር በተያያዘ መሆኑን፡፡

እስከ አሁንም ድረስ ትግሮችን ጨምሮ የተቀረውም ኢትዮጵያዊ "ክርስቲያን ነኝ!"ለማለት "አማራ ነኝ!" የሚባል የቃል አጠቃቀም መኖሩንና ካሉ ሌሎች መረጃዎች በተጨማሪ ከዚህም ትውፊታዊ የቃል አጠቃቀም ክርስትናን ያወጁት አክሱማውያኑ አማሮች እንደነበሩ መረዳት እንደሚቻል ምክንያቱም አክሱሞች በአብርሃ አጽብሐ (በ 4 ኛው መቶ ክ/ዘ) ይሁዲነት ቀርቶ ክርስትናን ብሔራዊ ሃይማኖት እንዲሆን በማወጃቸው ከአይሁድ ማኅበረሰብ ጋር ግጭት መነሣቱን እስከ ዮዲት ጉዲት መምጣት ድረስ አማሮቹ (አክሱማዊያኑ) በአሸናፊነት ተቆጣጥረውት መቆየታቸውን በዮዲት ጉዲት ዘመን ግን በመሸነፋቸው ዮዲት አማራውን ክርስቲያኑን ወይም አክሱማውያኑን ለማጥፋት ቆርጣ በመነሣቷ አክሱምና አካባቢዋ የነበሩትን አማሮችን ወይም ክርስትናን ያወጁትን አክሱማውያንን በጅምላ ከመፍጀት ጀምሮ የማረከቻቸውን ወደ ዓረብ ሀገራት ለባርነት እስከመሸጥ ድረስ ለ 40 ዓመታት ያክል ይሄንን ግፍ በስፋት ስትፈጽም መቆየቷን፡፡

በሷ ማሳደድ ምክንያት ወደ ሸዋ ተሰደው በነበሩ (በእርግጥ ሸዋ ልዩ ስፍራው የረር በመባል በሚጠራው ምሥራቅ አዲስ አበባ ላይ ባለ ተራራማ ስፍራ ላይ ከዚህ የስደት ዘመንም በፊት ከአብርሃ አጽብሐ እስከ አምሲ ድረስ ከሁለት መቶ ዓመታት በላይ የአክሱማውያን ማለትም የአማሮች መናገሻ እንደነበረች የታሪክ ሰነዶች፣ ቦታው ላይ ያለ የታሪክ አሻራና አሁንም ድረስ በዙሪያውና በአካባቢው ያሉ ጥንታዊ አብያተክርስቲያናት ያረጋግጣሉ)
ይህ እንዳለ ሆኖ በወቅቱ አክሱም የነበሩትና በሷ ምክንያት ተፈናቅለው ተሰደው ሸዋ መርሐቤቴ በነበሩ አማሮች (አክሱማዊያን) የመልሶ ማጥቃት ዮዲት ድል እስከተመታችበት ጊዜ ድረስ በርትታ ስትፈጽመው በነበረው የአማራን ዘር ማጥፋት ጥቃት ሳቢያና በወረራው ጊዜ አማራ በመሆን ብቻ ከሚፈጸም ከዮዲት የግድያ ጥቃት ለማምለጥ ለመትረፍ ሲሉ በርካቶች አማራነታቸውን በመካድ አገልጋዩን ለባርነት ተግዞ የመጣውን ጎሳ በመጥራት "ትግሬ ነኝ" ያሉና የተረፉም በርካቶች መኖራቸውን ነገር ግን ወረራው ለ 40 ዓመታት ስለቆየና ከዚያም በኋላ አማራ በመሆን የመጠቃቱ አደጋ ዳግመኛ ላለመከሰቱ እርግጠኛ ባለመሆናቸው ለመትረፍ ሲሉ የተላበሱትን ሐሰተኛ የትግሬነትን ማንነት ተላብሰው እንዲቀሩ እንዳስገደዳቸው፤ በእነዚህ ምክንያቶች አማራ ከአክሱምና አካባቢዋ ጠፍቶ መቅረቱንና ከዚያ በኋላ ያ ሀገር ትግሬ (ትግራይ) እስከመባል ደርሶ የትግሬ ሀገር መስሎ በትግሮች ሊሞላ እንደቻለ እነኝህን እነኝህን በመግለፅ ከዓመታት በፊት መጻፌ ይታወሳል፡፡

በነገራችን ላይ ይህ የዮዲት ጉዲት ታሪክ ትግሮች ከአክሱም ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌላቸው የሚያሳዩ የሚያረጋግጡ መረጃዎችን የያዘ የሀገራችን ታሪክ ስለሆነ ትግሮች የአማራን ታሪክ

ወርሰው የራሳቸው ለማድረግ በሰው ታሪክ ለመድመቅ የሚያደርጉትን ጥረት የሚያከሽፍ በመሆኑ በተለይም አሁን አሁን ይሄንን የዮዲት ጉዲት ታሪክ ጨምሮ ክብረነገሥትን እንዳለ "ያልነበረ ያልተፈጸመ ፈጠራ ነው!" በማለት በሰፊው ማስተባበልንና ማራከስን ተያይዘውታል፡፡

እንደነሱ አባባል ክብረነገሥት የዓረቦች ልብወለድ ድርሰት ነው፡፡ እንዲህ የሚሉበት ምክንያትም የክብረነገሥት የዓረብኛ ቅጅዎች በዓረቦች እጅ ያለ በመሆኑ ነው እንጅ "የአማራ ድርሰት ነው" ማለቱን ነበር የሚመርጡት፡፡ ክብረ ነገሥት ትክክለኛ ታሪክ እንጅ ዓረቦች አማራን ለማግነን ብለው ድርሰት ጽፈው የሰጡን ፈጠራ አለመሆኑን የሚያረጋግጠው እንደሚታወቀው ዓረቦች "ንግሥት ማክዳ ወይም ሳባ የእኛ ንግሥት ናት እንጅ የሐበሻ ወይም የኢትዮጵያ አይደለችም!" የሚሉ ሆነው እያለ ክብረ ነገሥት ግን ማክዳን ወይም ሳባን የዓረብ ምድርን ጨምራ ትገዛ የነበረች ኢትዮጵያዊት ወይም ሐበሻ ንግሥት መሆኗን የሚተርክ የታሪክ መጽሐፍ በመሆኑ ዓረቦች "ታሪካችን ነው!" የሚሉትን በሌላ እንዲወሰድባቸውና ሌላው እንዲገነበት የራሳቸውን ታሪክ የኢትዮጵያውያን እንደሆነ አድርገው ጽፈው ሊሰጡ የማይፈቅዱ መሆናቸውን በመረዳት በቀላሉ ክብረ ነገሥት አማራን ለማግነን ለመካብ የተጻፈ የዓረቦች ድርሰት አለመሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ንግሥተ ሳባ ወይም ማክዳ ኢትዮጵያዊት ወይም ሐበሻ ለመሆኗ ከዚህ ቀደም ጠንካራና ተጨባጭ መረጃዎችን መስጠቴ የሚታወስ ነው፡፡ እናም የትግሮቹ ጥረት ከንቱ ነው፡፡ የሚገርሙኝ ክብረ ነገሥትን የፈጠራ ታሪክ እንደሆነ ለማስመሰል ከሚደረገው ጥረት ጀርባ ማን እንዳለ ሳይገባቸው አብረው የሚያራግቡ ማስተዋል የሌላቸው የእኛ ሰዎች ናቸው፡፡ ትግሮች ብቻ አይደሉም ሌሎችም በጠባብ የጎሳ ፖለቲካ (እምነተ አሥተዳደር) ታንቀው የታሪክ ዝርፊያ መፈጸም የሚፈልጉ ወይም የጥፋት ዓላማቸውን ማሳካት የሚፈልጉ የታሪክ ቀበኞችም ሁሉ የዚህ የጥፋት ዘመቻ አካል ናቸው፡፡

ቀደም ሲል የጠቀስኩትን የትግሬ ታሪክ ከጻፍኩ በኋላ ያ ማንነታቸው ተደብቆ ካለበትና ደብቀው ከያዙት ከእነሱ አልፎ በሌላው ኢትዮጵያዊ ዘንድም እንዲታወቅ በማድረጌ ያፈሩ የተሸማቀቁ ትግሮች በስርቆት "የትግሬ ማንነት ነው!" ያሉትን ከፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት ጋር የተደረገ ቃለምልልስ በማስመሰል ተጨንቀው ተጠበው ትግሬ ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ቃል በማፈላለግና ከዚህ ቀደም ተሰምቶ ተጽፎም የማይታወቅ ተረት በመፈልሰፍ "ትግሬ የሚለው ቃል የመጣው ታይገር (ነብር) ተጋሩ ከሚለው ቃል ነው..." እያሉ በመቀባጠርና አማራን "ከአገውና ከቅማንት የተገኘና ጥንታዊ ማንነት የሌለው ዘር ነው፣ አምሐራ ማለት ነጻ ሕዝብ ማለት ነውና ከባርነት ነጻ ያወጣነው እኛ ነን..." በማለት በፈጠራ ወሬ ለመዝለፍ በመሞከር በቅድመ ታሪክ ላሉ ባለቤታቸው በግልጽ ለማይታወቅ ማንነቶችና ታሪኮች ባለቤቱ ማን እንደሆነ ለመገመት ከባሕል፣ ከቋንቋ፣ ከመፍለቂያ፣ ከሥነልቡና፣ ከባሕርይና ከሌሎች ተጨባጭ የማንነት መለያዎች ላይ በመመሥረት አንድን ታሪክ ወይም እሴት የማን እንደሆነ ለመገመት ወይም ለመበየን ከሚታዩ ወይም ሊታዩ ከሚገባቸው ጠቋሚ የማንነት መለያዎች ላይ በመመሥረት በታሪክ ተመራማሪዎችና በነገረ መለኮት ምሁራን ዘንድ በቅድመ ታሪክ ዘመን "ኢትዮጵያን ቶ ኔቶር (የእግዚአብሔር ሀገር) ብሎ ይጠራት የነበረው ዓረቦች ወደ ግብጽ ከመግባታቸው በፊት ግብጽን መሥርቶ ይኖርባት የነበረው ጥቁር ኩሻዊ የግብጽ መሥራች ሕዝብና ጥቁር ፈርኦኖች፣ በኋላም ይሄው ሕዝብ ከግብጽ ፈልሶ ወደ ሁለት የተለያየ አቅጣጫ በማምራት ግማሹ ቶ ኔቶር (ሀገረ እግዚአብሔር) ብሎ ይጠራት ወደነበረችው ሀገር ኢትዮጵያ መጥቶ የአክሱምን የኑቢያን የሜርዌን ሥርዎ መንግሥታት መሥርቶ የነበረው, ግማሹ ደግሞ ወደ ባቢሎን ተሻግሮ ባገኘው ሰፊ ሜዳ ላይ የጠፋችውን ባቢሎንንና ሰማይ ጠቀስ ሕንፃዋን (ጥቅመ ሰናኦርን) ገንብቶ የነበረው ያ ምንጩ ግብጽ የሆነው ጥቁር ኩሻዊ ሕዝብ፤ እዚህ ኢትዮጵያ የመጣው በኋላ ላይ ሳባውያኑ ተዋሕደውት በኩሻዊነቱ ላይ ሴማዊ ማንነትም ሊይዝ የቻለው ጥንታዊ ሕዝብ ዛሬ አማራ ተብሎ የሚጠራው ሕዝብ ሳይሆን እንደማይቀር ወይም እነደሆነ የማንነት እሴቶቹ ወይም መለያዎቹ ይጠቁማሉ!" እየተባለ የሚነገረውን ታሪክ አንድ ሳያስቀሩ በሙሉ ሊታዩ የሚገባቸውን መለኪያዎች ጨርሶ ግምት ውስጥ ባለማስገባት ዐይን ባወጣ ቅጥፈትና አስገራሚ የድንቁርና ድፍረት የትግሬ ታሪክ እንደሆነ አስመስለው እጅግ አስቂኝ በሆነ መልኩ በመተረክ የሕፃናት ተረታቸውን በመድረስ ያለባቸውን የሥነልቡና ቀውስ ሕመምና ስብራት ለማከም ለመጠገን ጥረት አደረጉ፡፡

ነገር ግን የአዋቂ ሱሪ ለልጅ አይገጥምም አያምርምምና የሰው ወርቅ አያደምቅምና በዚህ የልጆች ተረታቸው የነሱን ቢጤ ጎጋና ጅል ያጃጅሉ እንደሆነ ነው እንጅ አስተዋይና አዋቂ የሆነውስ የለበሱትን የሰው የታሪክና የማንነት ሱሪ ከባሕላቸው፣ ከቋንቋቸው፣ ከምንጫቸው፣ ከሥነልቡናቸው፣ ከማንነታቸው ወዘተረፈ.

ላይ በመነሣት ለመገመት ከሚረዱ መለኪያዎች አንጻር ትግሮችን ሲለካቸው ሲፈትሻቸው ቋንቋቸው ዓረብኛ የገነነበት ሴማዊ፣ ምንጫቸው ከየመን መሆናቸው ስለሚታወቅ "የኛ ነው!" ያሉት መሠረቱ ኩሽ የሆነ ሕዝብ ታሪክ የነሱ አለመሆኑን በቀላሉ ይገነዘባልና በዚህ አዲስ የፈጠራ ተረታቸው ሊያታልሉት አይችሉም፡፡ ከዚህ አንጻር ድካማቸው ከንቱ በመሆኑ እጅግ ያሳዝኑኛል፡፡

ይህ ከንቱ ጥረታቸውም ያለባቸውን የሥነልቡና ቀውስ ስብራትና ሕመማቸውን ያባብሳል እንጅ የሚረዳቸው አንዳችም ነገር የለምና በዓለም ውስጥ ካሉ ሀገራትና ሕዝቦች እኛን ጨምሮ ከአንድ እጅ ጣት ካልበለጡ ሀገራት ሕዝቦች በስተቀር ሁሉም አንዱ በሌላው በመገዛቱ ባሪያ ያልነበረ የባርነት ታሪክ የሌለው የለምና ባሪያዎቻችን የነበሩና ለባርነት ተግዘው ከየመን ያስገባናቸው መሆናቸውን በማሰብ ባርነት የተፈጥሮና በእነሱ ላይ ብቻ የደረሰ ነገር እንደሆነ አድርገው እያሰቡ ባይቆስሉ ልቡናቸው ባይታወክ ባይጨነቁ መልካም ነው ልላቸው እወዳለሁ፡፡

እነሱ ግን መቸም ሐፍረት የምትባል ነገር አልፈጠረባቸው አይደል! ከዚህ ተረት መፈጠር በኋላ በተረት የፈጠሩትን ሥያሜ እውነት አድርገውት በየጽሑፉ፣ በየብዙኃን መገናኛው፣ በሌላም ማኅበራዊ መድረክና ግንኙነት ማንነታቸውን የምትገልጸዋን "ትግሬ" የምትለዋን ስማቸውን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለማጥፋት ቆርጠው በመነሣት ካፋቸው የሚሰማው ቃል "ተጋሩ" የሚለው አዲሱ የፈጠራ ስም ብቻ ሆኗል፡፡ እርግጠኛ ሆኘ የምነግራቹህ ከጥቂት ጊዜ በኋላም "ትግሬ" ማለትን በአዋጅ ይከለክሉና በምትኩ "ተጋሩ" የሚለውን የፈጠራ ቃል እንድንጠቀም ያስገድዱናል፡፡

ታሪክ አሳፋሪም ይሁን የሚያኮራ አይሻሻልም! አይለወጥም! አይነካካም! ይሄንን ማድረግ የታሪክ ጥናት ሥነምግባርና መርሖ ፈጽሞ  አይፈቅድም!! እንደወረደ ነው ልንቀበለው የሚገባው፡፡ ምክንያቱም ምንም ይሁን ምን እውነቱ መጠበቅ አለበትና! ማንነት ማለት እሱ ነዋ! የፈጠራ ማንነት ሊኖር አይችልምና! እርግጥ ነው አሳፋሪው የታሪክ ወይም የማንነት ክፍል ላይመቸን ወይም ደስ ላያሰኘን ይችላል፡፡ የማይመቸን ቢሆንም እንኳ ጤነኛ አእምሮ ካለን፣ ለአመክንዮ ተገዢ ከሆንን፣ ለእውነታ ታማኝ ከሆንን፣ ኃላፊነት የሚሰማን ከሆነ፣ ሰብእናችን የተሟላ ከሆነ፣ ለኅሊናችን ክብርና ዋጋ የምንሰጥ ከሆነ እንዳለ እንቀበለዋለን እንጅ በምንም ተአምር የነበረውን አጥፍተን በቦታው የፈጠራ ተረት ልንተካበት አንነሣም፡፡

መፍትሔው ያ ደስ የማያሰኘን ያለፈ ነገር አሁን ባለው ማንነታችን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳያሳድር በሳል አመለካከት ይዞ መገኘት ነው እንጅ እውነታን መሸሽና መካዱ አይደለም፡፡ ይሄንን ማድረግ የባሰ የሥነ ልቡና መታወክን ያስከትላል፡፡ ምክንያቱም ይሄንን የምናፍርበትን ታሪክ ወይም ማንነት የሚያውቁ ሌሎች አሉና ነው፡፡ ይሄንን ማንነታችንን ፈጽሞ መስማት የማንፈልግ ከሆነና ሌላው ይሄንን በማወቁ የምንታወክ የምናር የምንበግን ከሆነ እነሱ በተለያየ መንገድ ይሄንን ጉዳይ ባነሡት ቁጥር ውስጣችን እየታወከ ከከባድ የሥነ ልቡና ያለመረጋጋት ችግር ወይም በሽታ ላይ ወድቀን በከባዱ ልንጎዳ እንችላለንና እውነታን ወይም ማንነትን ከመሸሽና ከመካድ ይልቅ አምኖ መቀበሉና አሁን ባለው አስተሳሰባችን ወይም ማንነታችን ላይ ግን አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳያሳድር ከፍታ ባለው የሰብእና ልቀትና በበሳል አመለካከት መከላከል ነውና መፍትሔው ለትግሬ ወገኖችን ይሄንኑ እመክራለሁ፡፡ ታሪካቹህን ማንነታቹህን አክብሩ ጠብቁትም፡፡ ይሄንን የምመክረው ለእነሱ ጤና በማሰብ ብቻ ሳይሆን የሀገር ታሪክ እንዲበረዝ እንዲከለስ እንዲቆነጻጸል ወይም ጨርሶ እንዲጠፋ ስለማልፈልግና ስለማልፈቅድም ነው፡፡ በመሆኑም ማናችንም ብንሆን የሥነልቡና መታወክ የማንነት ቀውስ የገጠማቸውና በቁማቸው በቅዠት ዓለም የተዋጡ ወገኖች አሁን በቅርብ የፈጠሩትን ተረት ይዘው "ተጋሩ ነን!" እያሉ እንዲቃዡብን በፍጹም በፍጹም ልንፈቅድ አይገባም፡፡ የብዙኃን መገናኛዎችም ይሄንን አዲስ የተፈጠረ ቃል በማስተናገድ በሀገር ታሪክ ላይ በደልና ክህደት እንዳይፈጽሙ አጥብቄ ማሳሰብ እወዳለሁ፡፡

ብዙዎቻችን ትግርኛ ከአማርኛ ይልቅ ለግእዝ የሚቀርብ ይመስለናል፡፡ እውነቱ ግን ይሄ አይደለም፡፡ እርግጥ ነው ትግርኛ አማርኛ ያልያዛቸውን የግእዝ ቃላትን ይዟል፡፡ እንደዚሁም ደግሞ ትግርኛ ያልያዛቸውን በርካታ የግእዝ ቃላትንም አማርኛ ይዟል፡፡ ትግርኛ የያዛቸውን የግእዝ ቃላት የወሰደው በቀጥታ ከግእዝ ሳይሆን ከዓረብኛ ነው፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ የዓረብን ምድር ማለትም የዛሬዎቹን ሳውዲዓረቢያንና የመንን ከፐርሺያ የዛሬዋ ኢራን ጋራ በመፈራረቅ ለረጃጅም ዘመናት ከመግዛቷ ጋር በተያያዘ ግእዝ በርካታ ቃላትን ለዓረብኛ አውርሷል፡፡ ለምሳሌ ማይ የግእዝ ቃል ነው፡፡ ውኃ በዓረብኛም ማይ ነው የሚባለው፡፡ ትግርኛ ማይ የሚለውን

ቃል የወሰደው በቀጥታ ከግእዝ ሳይሆን ከዓረብኛ ነው፡፡ ይሄንን ለማለት የሚያስችልበት ምክንያት ትግርኛ ከግእዝና አማርኛ ውስጥ በሌሉ መሠረታዊ የዓረብኛ ቃላት የተሞላ ቋንቋ በመሆኑ ነው፡፡ ግእዝ ወይም አማርኛ ለዓረቦቹ ያወረሰው ቃላትን ብቻ አልነበረም፡፡ ለቅኝ ገዦቻቸው (ለእኛ) በነበራቸው ጥላቻ ምክንያት በኋላ ላይ ቀላል የአጻጻፍ ስልት ያለውን የእኛን ፊደሎች ትተው የራሳቸውን ለመፍጠር ቻሉ እንጅ ቅኝ እንገዛቸው በነበረ ወቅት ፊደሎቻችንንም ለመውረስ ችለው ነበረ፡፡ ለዚህም በዓረብ ሀገራት ያሉ የአለት ላይ የግእዝ (ሳባ) ጽሑፎች ምስክሮች ናቸው፡፡

እርግጥ ነው እንደ የአክሱም ሕዝብ "አማራ ነን!" የሚለው ትውፊታዊ መረጃና የመጀመሪያው የትግሬ ንጉሥ ዐፄ ዮሐንስ 4ኛም ትግሬ ሆነው እያለ አማርኛን የመንግሥታቸው ቋንቋ አድርገው የሚጠቀሙበትን ምክንያት ሲናገሩ እንደገለጹትና ይሄንንም "አክሱም" በሚል ርእስ መጽሐፍ የጻፉትን የትግሬ ተወላጁን አቶ በላይ ግደይን ጨምሮ የተለያዩ የታሪክ ጸሐፍያን እንደገለጹት ሁሉ አማርኛ የአክሱማውያን የቤተመንግሥት የምሥጢር ቋንቋ ሆኖ ያገለግል የነበረ ቋንቋ ቢሆንም ትግሮች ወደሀገራችን የገቡት አማርኛ ገና የግእዝን ቦታ ሳይተካ ግእዝ የሀገራችን ብሔራዊ ቋንቋ በነበረበት ዘመን በመሆኑ ትግሮች እዚህ ሀገራችን ውስጥ የመኖራቸውን ያህል ባይሆንም ጥቂት ናቸው እንጅ ትግርኛ ከዓረብኛ ከወሰዳቸው የግእዝ ቃላት በተጨማሪ እንደ አማርኛ ሁሉ በቀጥታ ከግእዝ የተዋሳቸው ቃላቶችም አሉት፡፡ ግእዝ ከሦስት ሽህ ዓመታት በፊት ከደቡብ ዓረቢያ የገቡት ሳባዊያንና ነባሩ የኩሽ ነገድ ተዳቅለው የፈጠሩት ቋንቋ እንደሆነ የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ፡፡
ትግርኛ እዚህ ሀገራችን ውስጥ በመኖሩ ከአማርኛ በተዋሳቸው ቃላት ምክንያት ኩሻዊ ድምፆችንም ለማካተት ተገደደ እንጅ እንደ ሸ፣ ቸ፣ ኘ፣ ኸ፣ ዠ፣ ጀ፣ ጨ ያሉ የአማርኛ ኩሻዊ ድምፆች በቋንቋው ውስጥ የሉትም፡፡ የአክሱማውያኑ የቤተመንግሥት የምሥጢር ቋንቋ የነበረው አማርኛ ለእነ ሸ፣ ቸ፣ ኘ፣ ኸ፣ ዠ፣ ጀ፣ እና ጨ ድምፆቹ ፊደል ተቀርፆላቸው ብሔራዊ ቋንቋ ሆኖ የታወጀው የአክሱማውያኑ ልዑላንና ልዕልታት ሥልጣን "ለኔ ይገባል ለኔ!" በሚል ፀብ ሽኩቻና ግጭት የሚሸነፉቱ በየዘመኑ ግብጽ እየተሰደዱ እዚያ ተከማችተውና ተባዝተው ይኖሩ ከነበሩበት በዛግዌዎቹ አግባቢነት ጦር አደራጅተው ከዮዲት ጉዲት ጠንካራ ምት ውድቀት በኋላ እንደገና ተነሥቶ ለማገገም ጥረት ማድረግ ከጀመረ ሰላሣ ዓመት እንኳን ያላለፈውን የአክሱምን ገመምተኛ መንግሥት ወግተው ከጣሉ በኋላ ዛጉዌዎች የመንግሥትነትን ሥልጣኑን በያዙ ጊዜ ነው፡፡

ቋንቋው የቤተመንግሥት ቋንቋ መሆኑ በሕዝብ ዘንድ ተፈላጊ ስላደረገው በጣም ረጅም ባልተባለ ጊዜ ውስጥ ነው ቋንቋው ግእዝ በነበረ ሕዝብ ዘንድ ሊለመድና እያደርም የግእዝን ቦታ ለመያዝ የቻለው፡፡
ይሁንና አማርኛ የግእዝን ቦታ እንዳይይዝ የግእዝ መጻሕፍት "ዘጸሐፎ ለዘአጽሐፎ ወዘአንበቦ ወዘተርጎሞ ወለዘሰምዓ ቃላቲሁ ለዝንቱ መጽሐፍ ኅቡረ ይዘከረነ እግዚአብሔር በኪዳነ እገሌ ወእገሊት" የሚሉ ሆነው እያለ ከቤተክህነት በኩል በተለይም ከጎንደርና ከጎጃም ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን በኩል "ቅዳሴው፣ ገድላገድሉ፣ ድርሳናቱ፣ ተአምራቱ፣ ጸሎታጸሎቱ፣ መልክአመልኩ፣ የቅኔ መሥዋዕቱ በአማርኛ ከተደረገ ከቀረበ አይሰምርም! መሥዋዕቱም ጸበሉም አይለወጥም!" እስከማለት የደረሰ በመላ ግእዝን ከመጥፋት ለመታደግ በአማርኛ ላይ የመረረ የማጥላላት ዘመቻ ቢከፈትበትም አማርኛ ግእዝን አስረስቶ የሕዝብ ቋንቋ ከመሆን አልተገታም፡፡ በቤተክህነት ግን እስከአሁንም ድረስ ከስብከት ውጭ የቤተክህነት የአገልግሎት ቋንቋ ለመሆን አልበቃም፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሕዝበ ክርስቲያኑ ትምህርት ይወስድባቸውና በቃልኪዳናቸውም ይጠቀም ዘንድ ታስቦ በአንዳንድ ግለሰቦች ጥረት የገድላገድላት፣ የተአምራት፣ የድርሳናት ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ አማርኛ እየተተረጎሙ እየቀረቡ ቢሆንም ሌላው ማዕቀብ ግን ገና እንደተጣለበት ነው ያለው፡፡

ለነገሩ በእርግጥም አማርኛ ግእዝን እንዲተካ መፍቀድ አልነበረብንም፡፡ ይሄንን ማድረጋችን ሀገሪቱ ለረጅም ዘመናት ያካበተችውንና በግእዝ ተጽፈው ያሉትን የጥበብ፣ የፍልስፍና፣ የሕክምና፣ የመድኃኒት ቅመማ፣ የሥነ ምድር፣ የሕዋ ወይም የሥነ ፈለክ ምርምር፣ የሥነ ኪን፣ የዘመን አቆጣጠር፣ የምሕንድስና፣ የምክር፣ የሃይማኖት፣ የሥነ ምግባርና የግብረገብ ትምህርቶች ወዘተረፈ. የተጻፉበትና የተተነተኑበት ጥንታዊ የብራና መጻሕፍት ተደራሽ ሆነው እንዳንጠቀምባቸው የበኩሉን አሉታዊ አስተዋጽኦ አድርጓልና አማርኛ ግእዝን በመተካቱ ተጎዳን እንጅ የተጠቀምን አይመስለኝም፡፡

አማራ ቀድሞ የነበረ ጥንታዊና ገናና ዘር ቢሆንም ከጊዜ በኋላ ግን በነባራዊ ሁኔታዎች ምክንያት በዚህ ዘር ውስጥ ከሳባውያኑ በፊት 52 ኩሻውያን ነገሥታት የነበሩበትን የኩሽ ነጋሢ ዘር፣ በኋላም ከደቡብ ዓረቢያ ተሻግረው ከነባሩ የኩሽ ዘር ጋር ተቀላቅለው 22 ነገሥታት የወጡበትን ከንግሥት ማክዳ ወይም ሳባ

በፊት የነበረውንና እሷ የመጨረሻ የሆነችበትን የሳባውያንን እና ከንግሥት ማከዳ ልጅ ከቀዳማዊ ምኒልክ የሚጀምረውንም ሰሎሞናዊ የነገሥታት ዘር በውስጡ በአንድ ላይ አዋሕዶ የያዘ ዘር ሊሆን ችሏል፡፡
ወደ ቋንቋ ጉዳይ ስመለስ አማርኛ ለግእዝ ከትግርኛ ይልቅ ያለውን ቅርበትና ትግርኛ ደግሞ ምን ያህል እንደሚርቅ የሚያሳዩ አንዳንድ ነገሮችን ልጠቃቅስና ጽሑፌን ልጨርስ፡፡

ግእዝና አማርኛ የየግልና የጋራ የግእዝ ቤት ግሶች (በመጀመሪያ የፊደላት ተርታ የሚያልቁ ግሶች) በብዛት ሲኖሯቸው ትግርኛ ግን ከእነሱ እንዳለ ተውሶ የወሰደው ቃል ካልሆነ በስተቀር በቋንቋው የሰዋስው ሥርዓት መሠረት አንድም እንኳ እንዲህ ዓይነት ግስ የለውም፡፡

ምሳሌ፦ ቀደሰ፣ ሰገደ፣ ፈወሰ፣ ቀተለና ገደለ፣ መተረ፣ ነገረ፣ ዘመረ፣ ፈቀደ፣ ወረደ፣ መከረ፣ ወለደ፣ ሰቀለ፣ ሠየመ፣ ሰመረ፣ ሠወረ፣ ነደደ፣ መሰለ፣ ደነደነ፣ መዘመዘ፣ ገነፈለ፣ ወዘወዘ፣ ሰበሰበ፣ ሰነጠቀ፣ ወገረ፣ ገሠሠ፣ ፈረደ፣ ነገደ፣ ደፈነ፣ ነቀለ፣ ነደፈ፣ ጨከነ፣ መለሰ፣ ከነከነ፣ ነቀነቀ፣ ወረወረ፣ አመሰገነ፣ መከነ፣ ወገነ፣ ደከመ፣ ለወጠ፣ ወረወረ፣ ረፈረፈ፣ ተወ፣ ሰጠ፣ ቸረ እነኝህና እነኝህን የመሳሰሉ የጋራ እና የየግል ሌሎች በርካታ ግሶችም ሲኖሯቸው ትግርኛ ግን ወረደ የሚለውን ያጣምምና ወሪዱ፣ ሰቀለ የሚለውን ሰቂሉ ሌሎቹንም እንደዚሁ የግእዝ ቤት የነበሩትን ፊደሎች ወደ ሳልሥና ወደ ካዕብ እየቀየረ አወላግዶ ይጠራቸዋል እንጅ በትግርኛ ውስጥ የግእዝ ቤት ግስና ቃል የለም፡፡ እንዲኖርም የቋንቋው የሰዋሰው ሕግ አይፈቅድም፡፡ በዚህም ትግርኛ ምን ያህል ከግእዝና አማርኛ የራቀ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተጨማሪም ትግርኛ ከዓረብኛ እንደመውጣቱ በርካታ የጉሮሮ ድምፆች ሲኖሩት ግእዝና አማርኛ ግን እንደ ትግርኛ ያሉ የጉሮሮ ድምፆች የሏቸውም፡፡ ትግርኛ በግእዝና አማርኛ ውስጥ በሌሉ በርካታ የዓረብኛ ድምፆቹ ምክንያት ትግርኛ ተናጋሪዎች ግእዝንም ሆነ አማርኛን ለማንበብ ለማድመፅ (በድምፅ ለማለት) ይቸገራሉ፡፡ ከነአካቴውም በትክክል ሊጠሯቸው የማይችሏቸው በርካታ የግእዝና የአማርኛ ቃላቶችና ግሶችም አሉ፡፡

ቃላቶቹንና ግሶቹን ሲጠሯቸው ማለትም ሲያደምጿቸው በቃላቶቹና በግሶቹ ያሉ ፊደላቶችን ወይም ድምፆችን ሳድሱን ሳብዕ፣ ሳብዑን ሐምስ፣ ካዕቡን ሳብዕ፣ ግእዙን ካዕብና ሳብዕ እያደረጉ ነው የሚያነቡት ወይም የሚያደምፁት፡፡ ይሄም የአነባበብ ችግራቸው ሊባል ያልተፈለገን የሰዋስውና የትርጉም ስሕተት እንዲፈጥሩ ያደርጋቸዋል፡፡ አስተካክለው ለማድመፅ አፋቸው እሽ አይላቸውም አይታዘዝላቸውም፡፡ አማርኛ ተናጋሪ በሆኑት ላይ ግን ይሄ ችግር የለም፡፡ ቃላቶቹን ወይም ግሶቹን አስተካክለው ነው የሚያደምጿቸው ወይም የሚያነቧቸው፡፡

በዚህ ምክንያት ትግርኛ ተናጋሪዎቹ ከቤተክርስቲያን የአብነት ትምህርቶች አንዱና ግእዝን ማጥኛ ወይም መማሪያ የሆነውን የቅኔ ትምህርትን አይወዱትም፡፡ ቅኔ ቤት ገብተውም አይማሩም፡፡ ከተማሩም ግሦቹን እያወላገዱ በመግሰስ የሰዋስውና የትርጉም ስሕተት እየፈጠሩ እንደነገሩ ሆነው ይወጣሉ እንጅ ግእዙ እንደሚለው ቃላቶቹን በትክክል እየጠሩ ወይም እያደመፁ አጥንተው አይደለም የሚወጡት፡፡

ከትግርኛ በተጨማሪ አማርኛ መናገር የሚችሉቱ ትግሮች ግን ይህ ችግር ብዙም አይስተዋልባቸውም፡፡ አማርኛ መቻላቸው ግእዝ ቃላትን በትክክል ለመጥራት (ለማድመፅ) እንዲችሉ ሲያደርጋቸው ይታያል፡፡ ትግሮቹ ግእዝን መማር በሚፈልጉ ጊዜ ግእዝ በአማርኛ በኩል እንዲቀርቡት ሲያስገድዳቸው ይታያል፡፡ አንድ ምሳሌ ብጠቅስ "ሰለም ለኪ እንዘ ንሰግድ ንብለኪ" የሚለውን ቃል ትግሮቹ ሲያነቡት "ሰላም ለቺ እንዝ ንሰግድ ንብለቺ" በማለት ኪን ወደ ቺ ለውጠው ነው የሚያደምፁት፡፡ ይህ ችግራቸው ኪ ባለችበት ቃል ሁሉ አለ፡፡ ቺ ኩሻዊ የአማርኛ ድምፅ ነው የትግርኛ ድምፅ አይደለም፡፡ ነገር ግን ግእዝ ትግርኛ ተናጋሪዎችን የግእዝ ቃላትን በትክክል ማድመፅ ማለትም መጥራት ይችሉ ዘንድ በአማርኛ በኩል እንዲመጡ ስለሚያስገድዳቸው በቋንቋቸው ውስጥ የሌሉትን አማርኛ ድምፆችን በግድ ሲያስጠሯቸው ይስተዋላል፡፡

አማርኛ የግእዝ ፊደላትን (ፊደላቱ የግእዝ ይሁኑ የአማርኛ ራሱ ብዙ አከራካሪ ነገር አለው) ይሁንና አማርኛ በሙሉ ፊደላቱን ሲጠቀም፡፡ ትግርኛ ግን አብዛኞቹን ሞክሸ ፊደላቱን አይጠቀምም፡፡ የወሰዳቸውን ፊደሎችም ቅጽል በማድረግ የተለየ ቅርጽ ሰጥቶ ነው ከግእዝና አማርኛ ለተለዩ ድምፆቹ የፊደል ውክልና እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚጥረው፡፡ የግእዝንና የአማርኛን የአባትና የአንድያ ልጅነት ወይም ቀዳሚና ተከታይ የማይታወቅ የመንትያነት ቁርኝት ጥብቀትን ለመግለጽም "ለአማርኛ ግእዝ ነው ዳኛ!" ይባላል፡፡

አክሱም የትግሬ የሚመስላቸው ሰዎች ቅዱስ ያሬድ አክሱማዊ ነው ሲባል ትግሬ ይመስላቸዋል፡፡ በእርግጥ ቅዱስ ያሬድ በተነሣበት ዘመን ትግሮቹ ወደ ሀገራችን ከገቡ ብዙ የቆዩ ባይሆኑም እዚህ ሀገራችን ውስጥ ነበሩ፡፡ ይሁንና ከዓመታት በፊትም እንደገለጽኩት ቅዱስ ያሬድ አማራ እንጅ ትግሬ አይደለም፡፡ ይሄውም ይታወቅ ዘንድ የዜማ ምልክቶቹን ሥያሜዎች ቅናት፣ ድፋት፣ ደረት፣ ጭረት፣ ይዘት፣ አንብር፣ ሒደት፣ እርክርክ፣ ድርስ፣ ቁርጥ ብሎ በመሠየም አማርኛ አድርጓቸዋል፡፡ ቅዱስ ያሬድ አማራ ለመሆኑ ይሄ ግልጽ መረጃ የማይበቃው ካለ ራሱን ቅዱስ ያሬድን ጎንደር ተሠውሮ ካለበት ቅዱስ ቦታ ደብረ ሐዊ ከተባለው ዋሻ (የማያምኑ ወገኖች ያረፈበት ቦታ ይሉታል) ሔዶ በሱባኤ ሊጠይቀውና ሊያረጋግጥ ይችላል፡፡ ቅዱስ ያሬድ ጌታ ለፍርድ እስኪመጣ ድረስ እንደማያርፍ ወይም እንደማይሞት በወንጌሉ ላይ እንደተናገረለት (ዮሐ. 21: 21-23) ጌታ ይወደው እንደነበረው ሐዋርያ ዮሐንስ ተሠወረ እንጅ አላረፈም፡፡ ይቆየን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለ ወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር አሜን ወአሜን ለይኩን ለይኩን!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው
amsalugkidan@gmail.com

**http://www.ethiopanorama.com**